**የ “ታንክስጊቪንግ” መገጣጠሚያ ኮንፈረንስ**
**መልእክቶች አውትላይን**
**ሕዳር 18-21፣ 2018**

**አጠቃላይ ርዕስ፦**
**ሁሉን-ያካተተው ክርስቶስ**
**በማቴዎስ እንደተገለጠው**

መልእክት አንድ

**እንደ ሕያዉ ኮከብ የሰማያዊው ክርስቶስ**
**የአሁንና የዳበረው፣ ቅጽበታዊው እና ሕያዉ ራእይ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ማቴ. 2፥1-12፤ ዘኍ. 24፥17፤ ዘፍ. 1፥14-19፤ ዳን. 12፥3፤
ራእ. 1፥16፣ 20፤ 2፥1፣ 28፤ 3፥1፤ 22፥16፤ 2 ጴጥ. 1፥19፤ ዘፍ. 22፥17፤ ይሁ. 12-13

**I. ኢየሱስ በቤተልሔም ከተወለደ በኋላ፣ ከምሥራቅ የመጡ ሰብአ ሰገል “የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ኮከቡን በምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና” (ማቴ. 2፥2) እያሉ ኢየሩሳሌም ደረሱ፤ ይህ በዘኍልቍ 24፥17 “ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል” የሚለው ቃል ፍጻሜ ነው፤ ይህ ኮከብ ክርስቶስን ያመለክታል፦**

ሀ. ሰብአ ሰገል “ኮከቡን አይተን” እንጂ “ኮከብ አይተን” ወይም “ኮከብን አይተን” አላሉም፤ ኮከቡ ሰማያዊው ክርስቶስ ነው።

ለ. በማቴዎስ 2፥2 ላይ የተነገረው ኮከብ ለእነዚህ የተማሩ ሰዎች ታይቷል፤ ከእስራኤል ሕዝብ ለማንም አልተገለጠም፤ አይሁዶች ክርስቶስን የሚመለከቱ ቅዱሳት መጻሕፍት ነበራቸው፣ የት እንደሚወለድም ያውቁ ነበር (ቁ. 4-6)፣ ሰብአ ሰገል ግን የክርስቶስን ኮከብ አዩ።

ሐ. አይሁዶች ክርስቶስ የት እንደሚወለድ በፊደላት የሆነ እውቀት ነበራቸው (ሚክ. 5፥2)፣ ነገር ግን እነዚህ ከምሥራቅ የመጡ የተማሩ ሰዎች የእርሱን ሕያው ራእይ ተቀበሉ፤ በመጨረሻም፣ ኮከቡ ክርስቶስ ወደ ነበረበት ቦታ መራቸው (ማቴ. 2፥1-12)።

መ. ክርስቶስ እውነተኛው ፀሐይ ነው (ሚል. 4፥2)፣ ነገር ግን በትክክል ለመናገር፣ በሌሊቱ ዘመን እንደ ፀሐይ አይገለጥም፤ ይልቁንም እንደ ኮከብ ያበራል (ራእ. 2፥28)፤ ኮከብ በሌሊት ያበራል፣ ነገር ግን ቀን እየመጣ እንደሆነ ያመለክታል (ሮሜ 13፥11-14)።

ሠ. ክርስቶስ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲመጣ፣ እንደ ኮከብ በገሃድ ተገለጠ፣ ለሁለተኛ ጊዜ ሲመጣ ግን፣ ለድል ነሺዎቹ፣ የእርሱን መምጣት ለሚጠባበቁት የንጋት ኮከብ ይሆናል (ራእ. 2፥28፤ 22፥16)፤ ለሌሎች ሁሉ ክርስቶስ እንደ ፀሐይ ኋላ ላይ ይገለጣል (ሚል. 4፥2፤ ተዛ. ማቴ. 13፥43)።

**II. ክርስቶስን ማግኘት ሕያው የሆነ ጉዳይ መሆኑን ማቴዎስ 2፥1-12 ይገልጣል፤ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሯዊ እውቀት ጉዳይ ብቻ አይደለም፦**

ሀ. ኮከቡ በቅድስቲቱ ምድር ካለው ከመቅደሱ፣ ከአይሁድ ሃይማኖት ማዕከል፣ ከካህናቱ፣ ከጻፎች፣ ከፈሪሳውያን እና ከሃይማኖተኞች ሁሉ ርቆ ተገለጠ፤ በምትኩ፣ በአረማውያን ምድር የክርስቶስን አንዳች ነገር የሚያሳይ ኮከብ ነበር።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስን በእጃችን መያዝና ክርስቶስ በቤተልሔም ይወለዳል በማለት ሚክያስ 5፥2ን ማንበብ ብቻ፣ አይሠራም፤ መጽሐፍ ቅዱስ ሊኖረን ይችላል፣ ነገር ግን ሰማያዊው ኮከብ ሊያመልጠን ይችላል።

ሐ. ኮከቡ አሮጌ እና ሙት የሆነ የቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሯዊ እውቀት፣ የሚክያስ 5፥2 ሙት የሆነ እውቀት ሳይሆን፣ ሕያዉ መገለጥ፣ ሕያዉ ራእይ ነው፤ ዛሬ የሚያስፈልገን የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ብቻ ሳይሆን ሰማያዊው ራእይ፣ የአሁንና የዳበረው፣ ቅጽበታዊ ራእይ፣ ሕያዉ ራእይ፣ የሰው ፅንሰ-ሀሳቦች ፈጽሞ ሊያስተምሩት የማይችሉት ራእይ ነው።

መ. የቅዱሳት መጻሕፍት እውቀት ቢኖረንም፣ ኢየሱስ ወዳለበት ጎዳና እና ቤት የሚመራን ቅጽበታዊ፣ የአሁንና የዳበረ፣ ሕያው ኮከብ ያስፈልገናል።

ሠ. ሕያው የሆነውን ራእይ ከተቀበሉ በኋላ፣ ሰብአ ሰገል በሰዋዊ ፅንሰ-ሀሳባቸው ተሳሳቱ እና ወደ አይሁድ ሕዝብ ዋና ከተማ፣ ንጉሡ በዚያ እንደሚሆን ወደ ሚገመትበት ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ፤ መሳሳታቸው ብዙ ወንዶች ልጆች እንዲገደሉ አደረገ—ማቴ. 2፡16።

ረ. ኢየሩሳሌም በደረሱና የአይሁድ ንጉሥ ወዴት እንደሚወለድ በጠየቁ ጊዜ፣ “ንጉሡ ሄሮድስም ሰምቶ ደነገጠ፥ ኢየሩሳሌምም ሁሉ ከእርሱ ጋር” ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል—ቁ. 3፦

1. ይህንን ዜና በሰሙ ጊዜ፣ ደስ ሊሰኙ ይገባ ነበር፤ በምትኩ፣ ተረበሹ፤ ይህ በሌላ በምንም ምክንያት ሳይሆን አዳኙን በእውነት ካለመፈለጋቸው የተነሣ ነበር—ተዛ. ምሳ. 4፥23።
2. በጌታ የሚያምን ሰው በውስጣዊ ስሜቶቹ እንደ ፍቅር በጌታ ካልተነካ፣ ክርስቲያን ተብሎ ሊጠራ አይገባውም—2 ጢሞ. 4፥8፤ ማር. 12፥30፤ 1 ቆሮ. 2፥9።
3. ጌታ እንዲመጣ የሚጠባበቅ ወይም እንደሚነጠቅ የሚጠባበቅ ክርስቲያን ይህንን እንደ ማስጠንቀቂያ ሊወስደው ይገባል—2 ጢሞ. 4፥8፤ ቲቶ 2፥13፤ ራእ. 2፥28፤ 22፥20፤ ማቴ. 24፥40-44፤ 25፥8-13።

ሰ. ሰብአ ሰገል በቅዱሳት መጻሕፍት ከታረሙ በኋላ (2፥4-6)፣ ወደ ቤተልሔም ሄዱ (ቁ. 8-9)፣ ኮከቡም እንደገና ተገለጠላቸውና ክርስቶስ ወደ ነበረበት ቦታ መራቸው፣ “ኮከቡንም ባዩ ጊዜ በታላቅ ደስታ እጅግ ደስ አላቸው” (ቁ. 10)፦

1. ሰብአ ሰገል በቅዱሳት መጻሕፍት ታርመው ወደ ትክክለኛው መንገድ ሲመለሱ፣ ኮከቡ እንደገና ተገለጠላቸው፤ ሕያው ራእይ ሁል ጊዜ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር አብሮ ይሄዳል።
2. ካህናቱ ሕዝቡን ሕግን ያስተማሩ ነበሩ (ሚል. 2፥7)፣ ጻፎች ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚያውቁ ነበሩ (ዕዝ. 7፥6)፤ ካህናቱም ጻፎችም ስለ ክርስቶስ መወለድ እውቀቱ ነበራቸው (ማቴ. 2፥5-6)፣ ነገር ግን ከምሥራቅ ከመጡት ከሰብአ ሰገል በተለየ መልኩ ራእዩን አላዩም፣ ክርስቶስንም ለመፈለግ ልብ አልነበራቸውም።
3. የቱንም ያህል “መጽሐፍ ቅዱሳዊ” ብንሆን፣ የጌታን መገኘት ካጣን፣ ሙሉ በሙሉ ተሳስተናል፤ ጌታን ለማግኘት እና ለመከተል የአዲስ ኪዳን መንገድ ያለማቋረጥ በስውር መገኘቱ ውስጥ መቆየት ነው—ዮሐ. 5፥39-40፤ ኢሳ. 45፥15፤ ዘጸ. 33፥11፣ 14፤ ተዛ. 2 ቆሮ. 5፥16።
4. መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውቀት ማካበት ቀላል ነው፣ ነገር ግን ሕያው የሆነ ምሪት እንዲኖረን ከፈለግን፣ ከጌታ ጋር በቅርብ ግንኙነት ልንኖር ይገባል፤ ከእርሱ ጋር አንድ መሆን አለብን—ማቴ. 2፥10-14።
5. ሰብአ ሰገል ክርስቶስን አይተው ሰገዱለት፤ ከዚያም ወደ ሄሮድስ እንዳይመለሱ በሕልም በእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸው፣ ስለዚህ “በሌላ መንገድ” ወደ አገራቸው ሄዱ (ቁ. 12)፤ ክርስቶስን ካየነው በኋላ፣ ያንኑ የለመድነውን መንገድ፣ ከክርስቶስ ውጪ የሆነውን የሃይማኖትን መንገድ ፈጽሞ አንወስድም፣ ነገር ግን ሁልጊዜ መንገድ እንቀይራለን።

**III. የክርስቶስ ታማኝ ተከታዮች የክርስቶስ ብዜት ለመሆን ክርስቶስን እንደሚያበራው እና ሕያዉ ኮከብ የሚከተሉ የሚያበሩ እና ሕያዋን ከዋክብት ናቸው—ዳን. 12፥3፤ ተዛ. ዘፍ. 22፥17፦**

ሀ. ሕያዋኑ ከዋክብት እንደ እግዚአብሔር ኢኮኖሚ ማዕከላዊነት እና አጽናፍ-ዓለማዊነት የክርስቶስን ሰማያዊውን፣ ሕያውን፣ የአሁንና የዳበረውን እና ቅጽበታዊውን ራእይ ይከተላሉ—ሐዋ. 26፥16-18፤ ቆላ. 1፥17፣ 18።

ለ. ሕያዋኑ ከዋክብት የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚባርኩ ናቸው፤ ጌታን ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ ይበልጥ ባመሰገንን እና በእምነት ስለ እነርሱ መልካም በተናገርን መጠን፣ ራሳችንን ይበልጥ በእግዚአብሔር በረከት ሥር እናስቀምጣለን— ዘኁ. 24፥9፤ ዘፍ. 12፥2-3፤ 22፥17።

ሐ. ሕያዋኑ ከዋክብት ክርስቶስ እንደ ንጋት ኮከብ በየዕለቱ በልባቸው እንዲወጣ “በጨለማ ስፍራ ለሚበራ መብራት” ጥንቃቄ እንደሚደረግ ለቅዱሳት መጻሕፍት የትንቢት ቃል ይጠነቀቃሉ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ላለው ቃል ከተጠነቀቅን፣ እንደ ንጋት ኮከብ ከእውነተኛው መገለጡ በፊት ዛሬ ባለንበት የክህደት ጨለማ ውስጥ ለማብራት በልባችን ውስጥ የእርሱ መውጣት ይኖረናል—2 ጴጥ. 1፥19፤ ዮሐ. 6፥63፤ ራእ. 2፥28፤ 22፥16፤ 2 ጢሞ. 4፥8፦

1. በንጋት ኮከብ መርህ፣ አንድ ክርስቲያን በማለዳ መነሣት አለበት ምክንያቱም  ከጌታ ጋር ለመገናኘት (ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ለማድረግ፣ ለማወደስና ለመዘመር፣  መጽሐፍ ቅዱስን ከአገልግሎቱ ጽሑፍ ጋር እየጸለዩ-ለማንበብ እና ወደ ጌታ ለመጸለይ) ማለዳ ምርጡ ጊዜ ነው—መኃ. 7፥12፤ መዝ. 5፥1-3፤ 57፥8-9፤ 59፥16-17፤ 63፥1-8፤ 90፥14፤ 92፥1-2፤ 108፥2-3፤ 143፥8፤ ዘጸ. 16፥21።
2. ጌታ ለሚወዱት እና ነቅተው ለሚጠብቁት ከረዥም ቆይታ በኋላ ሲመለስ የመገኘቱን ትኩስነት እንዲቀምሱ ራሱን እንደ ንጋት ኮከብ በምሥጢር ይሰጣቸዋል—1 ተሰ. 5፥6፤ ራእ. 2፥28፤ 3፥2-3፤ 16፥15።

መ. ሕያዋኑ ከዋክብት ለእግዚአብሔር ግንባታ እጅግ ሕያው እና እጅግ የሚያበሩ እንዲያደርጋቸው ሰባት እጥፍ ያየለውን መንፈስ ይደሰታሉ፣ በእርሱም ይሞላሉ—3፥1፤ 4፥5፤ 5፥6።

ሠ. ሕያዋኑ ከዋክብት፣ ለኢየሱስ ምስክር ትኩሱንና የአሁኑን ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ያድሉ ዘንድ እስትንፋሳዊውን ክርስቶስ እንደ የእግዚአብሔር መልእክተኛ እና ከእግዚአብሔር እንደመጣው ትኩስ መልእክት የሚደሰቱ እና የሚለማመዱ የአብያተ ክርስቲያናት መልእክተኞች ናቸው—1፥16፣ 20፤ 2፥1፤ ሚል. 3፥1-3።

ረ. ሕያዋኑ ከዋክብት "በልባቸው ታላቅ ቁርጠኝነት" እና "ብዙ የልብ ምርምር" አላቸው፤ "ፀሐይ በኃይሉ በወጣ ጊዜ እንደሚሆን" እንዲሆኑ እና "በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ የሚያበሩ" እንዲሆኑ ከእግዚአብሔር ጋር አብረው ጠላቱን ለመዋጋት በአካሄዳቸው እንደ ከዋክብት የሆኑ የእግዚአብሔር አፍቃሪዎች ናቸው—መሳ. 5፥15-16፣ 20፣ 31፤ ዳን. 11፥32፤ ማቴ. 13፥43።

ሰ. ሕያዋኑ ከዋክብት በጨለማ ሲሄዱ ብርሃን ይሆንላቸው ዘንድ ያሕዌን የሚፈሩና የባሪያውን ድምፅ የሚሰሙ፣ በያሕዌ የሚታመኑ ናቸው—ኢሳ. 50፥10-11፤ መዝ. 139፥7-12፣ 23-24፦

1. ለራሳቸው ብርሃን የሚሠሩና በእግዚአብሔር ብርሃን ፈንታ ራሳቸው በሠሩት ብርሃን የሚሄዱ መከራ ይደርስባቸዋል—ኢሳ. 50፥11።
2. ይህ እግዚአብሔር በተሰጠን ብርሃን እንጂ ለራሳችን በሠራነው ብርሃን እንዳንሄድ ማስጠንቀቂያ ሊሆንልን ይገባል፤ "ኑ፣ በእግዚአብሔር ብርሃን እንሂድ"—2፥5።

ሸ. ሕያዋኑ ከዋክብት በእግዚአብሔር የመመለስ ሥራ ተከታዩን ፈጠራውን ጨምሮ በአራተኛው ቀን በተፈጠሩት በብርሃናቸው በሚገዙት ከዋክብት ተመስለዋል፤ ብርሃን ባለበት፣ ለሕይወት እድገት የሆነ መግዛት አለ—ዘፍ. 1፥14-19፦

1. በክብር በተለወጠበት ተራራ ላይ የጌታ ኢየሱስ ማብራት የመንግሥቱ በኃይል መምጣት ነበር፤ ይህ ማብራት በእርግጥ የሦስታንዱ አምላክ የሚገዛ መገኘቱ ነው—ማቴ. 17፥1-8፤ ማር. 9፥1-8።
2. የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ እግዚአብሔር አገዛዝ፣ እንደ እግዚአብሔር መንገሥ፣ ከሁሉም በረከቶቹ እና ድሰታዎቹ ጋር የጌታ ኢየሱስ ማብራት እና በእኛ ላይ በማብራት የጌታ ኢየሱስ መስፋፋት ነው።
3. መንግሥቱ የጌታ ኢየሱስ እውነታ ማብራት ነው፤ እርሱ በእኛ ላይ በሚያበራበት ጊዜ እና እኛ በዚያ ማብራት ሥር በምንሆንበት ጊዜ ሁሉ፣ ለሕይወት እድገታችን በውስጣችን በእግዚአብሔር አገዛዝ እና መንገሥ ሥር በመንግሥቱ ውስጥ እንሆናለን።

ቀ. በአሉታዊ ጎኑ፣ አንዳንድ "የሚንከራተቱ ከዋክብት" አሉ—ይሁ. 12-13፦

1. የሚከራተቱ ከዋክብት የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር የተሳሳቱት አስተማሪዎች፣ ከሃዲዎቹ፣ በሰማያዊው መገለጥ ውስጥ ባሉ የማይለዋወጡ እውነቶች ውስጥ በጽኑ እንዳልተተከሉ፣ ነገር ግን እንደ ከዋክብት በሆኑ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል እየተንከራተቱ እንደነበር ያመለክታል።
2. የሳቱት ከሃዲዎች ዛሬ የሚንከራተቱ ከዋክብት ናቸው፣ ነገር ግን በመጨረሻ ለዘላለም በተጠበቀላቸው ድቅድቅ ጨለማ ይታሰራሉ።
3. አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ግብ ሳይሆኑ የክርስቶስ አካል እውነታ ግብ ጋር ለመድረስ የከንውን ሂደት መሆናቸውን የማያስተምር ማንኛውም ሰው በአሁኑ ዘመን ያለውን የእግዚአብሔርን አገልግሎት ፍላጎት አይመጥንም፤ ለክርስቶስ አካል እውነታ ከአብያተ ክርስቲያናት ጋር መገጣጠም የሚከለክለን ማንኛውም ሰው የሚንከራተት ኮከብ ነው፤ እውነተኞቹ ከዋክብት ብዙዎችን ወደ ጽድቅ የሚመልሱ፣ ሰዎችን የማያስቱ ነገር ግን ወደ ቀናው መንገድ የሚመልሷቸው ናቸው።
4. ዛሬ ሕያዉ ኮከብ እና ሕያዋኑ ከዋክብት ከእኛ የራቁ አይደሉም—እንደ የክርስቶስ አካል ተግባራዊ መገልጦች በአጥቢያ አቢያተ ክርስቲያናት ውስጥ እና ከአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ናቸው (ራእ. 1፥11፣ 20)፤ በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የተወሰኑ ሕያዋን ከዋክብት አሉ፤ ከእነርሱ ጋር መገናኘት እና ከእነርሱ ጋር በኅብረት መቆየት ብቻ ያስፈልገናል፤ ኢየሱስ ወዳለበት ቦታ ይመሩናል።

በ. ጌታን ለመገናኘት፣ እርሱን ለማምለክ እና ፍቅራችንን ለእርሱ ለማቅረብ ሁልጊዜ በትክክለኛው መንገድ እንድንጠበቅ ጌታ ምሕረት ያድርግልን፤ እንደ ሕያዋኑ ከዋክብት የእርሱ ብዜቶች እንሆን ዘንድ ስለ ክርስቶስ አዳዲስ ግኝቶችን ለማግኘትና ለማድረግ ሕያዉን ኮከብ እንደሚከተሉት እንደ ሰብአ ሰገልጌታ ሁላችንን ያድርገን—ተዛ. ኤፌ. 5፥8-9፤ ኤር. 15፥16።

*© 2025 Living Stream Ministry*

## <u>የእግዚአብሔርን በረከት ለመቀበል የእግዚአብሔርን ሕዝብ መባረክ</u>

“የሚባርኩህንም እባርካለሁ፥ የሚረግሙንም እረግማለሁ”—ዘፍ. 12፥3
“የሚመርቅህ ሁሉ የተመረቀ ይሁን፥ የሚረግህም ሁሉ የተረገመ ይሁን”—ዘኁ. 24፥9

*CWWL, 1978,* vol. 1, “Fellowship with the Serving Ones, Volume One,” p. 203*:*
ስብሰባዎችን መንቀፍ በጌታ ዓይኖች ክፉ፣ ርኩስ ነው። ጌታ “ይህ አካሌ ነው። እናንተ ማን ናችሁ? ለቤተ ክርስቲያኔ ስብሰባ መለኪያ እንድታዘጋጁ መብት የሰጣችሁ ማነው?” ይላችኋል። ስለ ስብሰባው ነቀፋ ያለበትን ነገር ስትናገሩ፣ ወዲያውኑ አንድነቱን ታፈርሳላችሁ። ሌሎች ስለ መልካም ስብሰባ ያላችሁን አሳብ አይወዱትም እንበል። እናንተ ምን ትላላችሁ? ስብሰባውን አልወደው ይሆናል፣ ነገር ግን አንድም ቃል ለመናገር አልደፍርም ምክንያቱም ክፍፍልን ይፈጥራልና...ስብሰባውን አልወደውም ብዬ እናገር ዘንድ እኔ ማን ነኝ? የጌታ የምሕረት ማብራት ወደ እኛና ወደ ብዙ ውዶቹ ይምጣልን።

*Life-study of Exodus,* msg. 7, pp. 78-80
እግዚአብሔር ሕዝቡን በሚያያቸው መንገድ እንዳያቸው የረዳኝ ነገር በ 1940ዎቹ መጀመሪያ ላይ በሻንግሃይ ባለችው ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ስብሰባ ላይ ተከሰተ። በዚያ ስብሰባ ልምድ ያላት አንዲት አብሮ ሠራተኛ እኅት፣ በቤተ ክርስቲያን ዝቅ ያለ ሁኔታ ተረብሻ፣ በጌታ ፊት ስለ ቤተ ክርስቲያን ጮኸች። ከቤተ ክርስቲያን ጎስቋላ ሁኔታ የተነሣ አቃሰተች፣ ቃተተችም። ጸልያ ስትጨርስ፣ ወንድም ኒ፣ ቤተ ክርስቲያን ፈጽሞ ደካማ ወይም ዝቅ ያለች ሆና እንደማታውቅ ነገር ግን ሁልጊዜ ከፍ ያለች ስለመሆኗ ድንገት ጠንካራ በሆነ መንገድ ጌታን አወደሰ፣ አመሰገነውም። ጉባኤው ደነገጠ። ያኔ ወንድም ኒ በለዓም ስለ እስራኤል ልጆች  የተናገረውን ትንቢት ትርጉም እንድንረዳ ረዳን። በለዓም የእስራኤልን ልጆች እንዲረግም በባላቅ ተቀጥሮ ነበር። ነገር ግን በለዓም የእግዚአብሔርን ሕዝብ በመርገም ፈንታ ባረካቸው። በለዓም እግዚአብሔርን ወክሎ ሲናገር “በያዕቆብ ላይ ክፋትን አልተመለከተም፥ በእስራኤልም ጠማምነትን አላየም” አለ (ዘኁ. 23፥21)። በተጨማሪም፣ በዘኁልቁ 24፥5 በለዓም “ያዕቆብ ሆይ፥ ድንኳኖችህ፥ እስራኤል ሆይ ማደሪያዎችህ ምንኛ ያምራሉ!” ብሏል። በእነዚህ ጥቅሶች መሠረት፣ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ በደል ወይም ጠማምነት አላየም። በምትኩ፣ መልካምነትን፣ ውበትንና ቁንጅንና ብቻ አየ። ዛሬም ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ ሁኔታው ተመሳሳይ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ደካማ ወይም ሙት ናት አትበሉ። ይበልጥ ይህንን ባላችሁ መጠን፣ ይበልጥ ራሳችሁን በእርግማን ሥር ታደርጋላችሁ። ሆኖም፣ ጌታን ስለ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ካወደሳችሁትና ስለዚያም መልካም ከተናገራችሁ፣ ራሳችሁን ከእግዚአብሔር በረከት ሥር ታደርጋላችሁ። በቤተ ክርስቲያን ሕይወት በነበርኩባቸው ዓመታት ሁሉ፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን አሉታዊ በሆነ መንገድ ተናግሮ ከእግዚአብሔር በረከት ሥር የሆነ አንድም ሰው አላየሁም። በተቃራኒው፣ ቤተ ክርስቲያን ጎስቋላ፣ ዝቅ ያለች ወይም ሙት እንደሆነች የተናገሩ ሁሉ ከእርግማን በታች ሆነዋል። ቤተ ክርስቲያን የምትወደድና የእግዚአብሔር ቤት መሆኗን በማወጅ ስለ ቤተ ክርስቲያን አዎንታዊ በሆነ መንገድ የሚናገሩት በረከቱን ይቀበላሉ። ይህ አስተምህሮ ብቻ አይደለም፤ በብዙ ቅዱሳን ልምምድ ሊረጋገጥ የሚችል ምስክርነት ነው።

አንዳንድ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ተስፋ ስቆርጥና ስለ እርሷ አዎንታዊ በሆነ መንገድ ሳላስብ ስቀር፣ ጌታ በውስጤ እንድጠነቀቅ ያስጠነቅቀኛል። ወዲያውኑ፣ ጌታ እንዲያነጻኝ እጠይቀውና ቤተ ክርስቲያን እንዴት ድንቅ እንደሆነች ማወጅ እጀምራለሁ። ቤተ ክርስቲያን ብታስቸግረኝም እንኳን፣ አሁንም ቤተ ክርስቲያንን እወዳታለሁ። ይበልጥ በዚህ አዎንታዊ መንገድ በተናገርኩ መጠን፣ ይበልጥ በእግዚአብሔር በረከት ሥር እሆናለሁ።

ስለ ቤተ ክርስቲያን ትክክለኛው ቃል የማነው? የእናንተ ወይስ የጌታ? በዘላለም ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ድንቅ፣ ክብርትና እጅግ ከፍ ያለች ስለምትሆን፣ የጌታ ቃል ትክክል መሆኑ በዘላለም ውስጥ ይረጋገጣል። ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ የሰይጣን ክሶች በሙሉ ውሸቶች ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ጎስቋላ ወይም ሙት እንደሆነች መናገር ዲያብሎሳዊ ውሸት መናገር ነው። የሚታየው የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ውሸት ነው። ቤተ ክርስቲያን ቀዝቃዛ ወይም ሙት ወይም ዝቅ ያለች ናት እንደሆነች መናገር ውሸት ነው። ቤተ ክርስቲያን እጅግ ከፍ የተደረገችና እጅግ ሕያው ናት። ወንድም ኒ ስለ በለዓም ትንቢት ስለ ተናገረው ጠንካራ ቃል አመሰግናለሁ። ያ ቃል ስለ ቤተ ክርስቲያን አሁናዊ ሁኔታ ያለኝን ፅንሰ-ሃሳብ ሙሉ በሙሉ ለውጦታል። ያን ቃል ከተቀበልኩበት ጊዜ አንሥቶ፣ ቤተ ክርስቲያንን ሙሉ በሙሉ በተለየ ብርሃን አይቻታለሁ።

ጌታ ከሚያየው በላይ ጠለቅ ብላችሁ አትመልከቱ። በዘኁልቁ ባለው በበለዓም ንግግር መሠረት፣ ጌታ በያዕቆብ ላይ በደልን አላየም። ታዲያ፣ እናንተ እንዴት ልታዩ ትችላላችሁ? ከእግዚአብሔር የበለጠ ጠቢብ ወይም አስተዋይ ናችሁን? መጽሐፍ ቅዱስ ጌታ በእስራኤል ጠማምነት እንዳላየ ያውጃል። እናንተ ግን በቤተ ክርስቲያን ጠማምነት እንዳያችሁ ታውጃላችሁ። የቱን ማመን ትመርጣላችሁ? የጌታን እይታ ወይስ የእናንተን? ጌታ ስለ ቤተ ክርስቲያን ካለው አስተያየት ጋር ከቆምን፣ ከበረከት ወደ እርግማን ከመውደቅ እንጠበቃለን። ሁላችንም ቤተ ክርስቲያንን የምናይበትን እይታ በተመለከተ የምንጠነቀቅ እንሁን።

*© 2025 Living Stream Ministry*

መልእክት ሁለት

**ክርስቶስ እንደ ሐኪም እና ሙሽራው**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ማቴ. 9፥10-13፣ 15፤ ራእ. 19፥7-9

**I. የማቴዎስ ወንጌል ክርስቶስ ከሃይማኖት በተጻራሪ መሆኑን እና ክርስቶስን የሚመለከቱ ነገሮች ከሃይማኖት ውጭ መሆናቸውን ይገልጣል፦**

ሀ. የክርስቶስ ውልደት፣ የክርስቶስ መገኘት፣ የክርስቶስ መተዋወቅ እና ክርስቶስን መከተል ሁሉ ከሃይማኖት ውጭ ነበሩ—1፥18-23፤ 2፥1-12፤ 3፥1-12፤ 4፥12-22።

ለ. በሃይማኖት ውስጥ ነገሮችን በተአምራዊ መንገድ የማድረግ ማንኛውም ሃሳብ የዲያብሎስ ፈተና ነው—ቁ. 5-7።

ሐ. እንደ ሐኪም እና ሙሽራው፣ ክርስቶስ ከሃይማኖት በተጻራሪ ነው—9፥12፣ 15።

መ. ጌታ ኢየሱስ ለሃይማኖታዊ ወግ ግድ የለውም፤ ግድ የሚለው ለውስጣዊ እውነታ ነው—15፥1-20።

**II. ማቴዎስ 9፥10-13 ክርስቶስን እንደ ሐኪም ልንለማመደው እና ልንደሰተው እንደምንችል ያመለክታል፦**

ሀ. ሰዎች ለመንግሥቱ እንዲከተሉት በመጥራቱ፣ ጌታ ኢየሱስ ያገለገለው እንደ ሐኪም እንጂ እንደ ፈራጅ አይደለም።

ለ. የዳኛ ፍርድ በጽድቅ መሠረት ነው፣ የሐኪም ፈውስ ደግሞ በምሕረትና ጸጋ መሠረት ነው።

ሐ. በዚህ በተበላሸ ምድር ላይ ሰማያዊ መንግሥቱን መመሥረት የሚችልባቸው አዲስ እና ሰማያዊ ዜጎቹ ሆነን መልሰን እንቀናበር ዘንድ ክርስቶስ እንደ ሐኪም ሊያገለግል፣ ሊፈውሰን፣ ሊመልሰን፣ ሕያዋን ሊያደርገን እና ሊያድነን መጣ።

መ. "ነገር ግን ሄዳችሁ፦ ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም ያለው ምን እንደ ሆነ ተማሩ"—ቁ. 13፦

1. ጌታ ኢየሱስ መንፈሳዊ ሕመማችንን፣ የኃጢአት ሕመማችንን ይፈውሳል።
2. በኃጢአትና በሞት መካከል ሁሉም ዓይነት ሕመሞች፣ ደዌዎችና ድክመቶች አሉ።
3. ጌታ ኢየሱስ ኃጢአቶቻችንን ይቅር ይላል፣ በሁሉም መንገድ ይፈውሰንማል።
4. እንደ ኃጢአተኞች፣ ፈጽሞ ታምመናል፣ ምክንያቱም አካላዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሥነ ምግባራዊ እና አእምሯዊ በሆነ መልኩ የታመምን ነን፣ ነገር ግን ይቅር ባዩ እና ሐኪሙ ኢየሱስ ሕመማችንን ሁሉ መፈወስ ይችላል።
5. እንደ ሐኪማችን፣ ጌታ በዋናነት የሚፈውሰን መንፈሳችንን እና ነፍሳችንን እንጂ በዋነኛነት አካላችንን አይደለም።
6. ምንም እንኳን ጌታ አካላችንን ሊፈውሰን ወይም ላይፈውሰን ቢችልም፣ በሁሉም የመንፈሳችን እና የነፍሳችን ክፍሎች ሊፈወስን ሁልጊዜ ዝግጁ ነው።
7. እንደ ሐኪማችን የጌታ ፈውስ በዋናነት አካላዊ ሳይሆን መንፈሳዊ ነው፤ መንፈሳዊ ሕመማችንን የሚፈውሰው እርሱ ነው።

ሠ. የጳውሎስ በኋለኛው አገልግሎቱ የነበረው ልምምድ እንደ የአማኞች ሐኪም ስለ ክርስቶስ ተገቢ የሆነ አድናቆት እንዲኖረን ይረዳናል፦

1. በ 2ኛ ጢሞቴዎስ 4፥20 ጳውሎስ "ጥሮፊሞስን ግን ታሞ በሚሊጢን ተውሁት" ይላል።
2. ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ያለውን የቅርብ የሆነውን ሰው የፈውስ ጸሎት ሳያደርግለት እንደታመመ ተወው።
3. ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ከሆድ ሕመሙ ለመፈወስ የፈውስ ስጦታውን አልተጠቀመም (ሐዋ. 19፥11-12)፤ ይልቁንም ለመፈወስ ተፈጥሯዊውን መንገድ እንዲወስድ ጳውሎስ አዘዘው (1 ጢሞ. 5፥23)።
4. ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ጥቂት የወይን ጠጅ እንዲወስድ አበረታታው፣ ጥሮፊሞስንም በሚሊጢን ተወው።
5. ጳውሎስ አብሮ ሠራተኞቹን በጣም ሰብዓዊ በሆነ መንገድ ተንከባከባቸው።
6. ጳውሎስ በዚህ መንገድ እነርሱን የተንከባከበበት ምክንያት፣ በመከራ ጊዜ፣ ጳውሎስና አብሮ ሠራተኞቹ በውጫዊው ስጦታ ኃይል ሥር ከመሆን ይልቅ በውስጣዊው ሕይወት ማደብ ሥር ስለ ነበሩ ነው።
7. ውስጣዊው የሕይወት ማደብ በሕይወት የሆነ ከጸጋ ነው፤ ውጫዊው የስጦታ ኃይል ግን በኃይል—በተአምራታዊ ኃይል—የሆነ ከስጦታ ነው።
8. የጳውሎስ ልምምድ በአብዛኛው ዛሬ የክርስቶስ ፈውስ ለመንፈስና ለነፍስ መሆኑን እንድናይ ሊረዳን ይገባል።
9. ይህን ራእይ ካየን፣ በክርስቶስ እንታመናለን፣ እርሱንም እንደ ሐኪማችን እንለማመደዋለን።

ረ. እንደ ሐኪማችን፣ ክርስቶስ የመፈወስ ሥልጣን አለው፦

1. የእርሱ ፈውስ የኃይል ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሥልጣንም ነው።
2. እኛን ለመፈወስ በቀጥታ እኛን መንካት አያስፈልገውም።
3. አንድ ቃል መናገር ብቻ ያስፈልገዋል፣ ሥልጣኑም ከቃሉ ጋር እኛን ለመፈወስ ይመጣል—ማቴ. 8፥8።
4. ሐኪማችን በሥልጣኑ ይፈውሰናል።

**III. በማቴዎስ እና በራእይ ክርስቶስ እንደ ሙሽራ ተገልጧል—ማቴ. 9፥15፤ ራእ. 19፥7-9፦**

ሀ. ማቴዎስ 25፥1 ጌታ ኢየሱስን እንደ ሙሽራው የሚመለከት ተጨማሪ ቃል ነው፦

1. ይህ ጥቅስ ጌታ እንደ ሙሽራ፣ እጅግ ደስ እንደሚል እና እንደሚማርክ ማንነት ተመልሶ እንደሚመጣ ይገልጣል።
2. ክርስቶስ ሙሽራይቱ ትኖረው ዘንድ የእግዚአብሔር አካል መልበስ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጣል።
3. ስለዚህ፣ የክርስቶስ ሚና የሙሽራው ነው።
4. እንደ ሙሽራው፣ እርሱ ለድሰታችን ደስ የሚያሰኘው ማንነት ነው።
5. ክርስቶስን ሕይወትን ለመመለስ እንደሆነው እንደ ሐኪማችን ብቻ ሳይሆን በመገኘቱ ለሕያው ድሰታ እንደሆነው እንደ ሙሽራችንም ልናደንቀው ይገባል።

ለ. ራእይ 19፥7-9 ክርስቶስን እንደ ሙሽራው ይገልጣል፡-

1. እነዚህ ጥቅሶች ጌታ ኢየሱስ እንደ ሙሽራው በጉ እንደሆነ ይገልጣሉ።
2. ክርስቶስ እንደ በጉ እና እንደ ሙሽራው ቀርቧል።
3. በዮሐንስ ወንጌል፣ ክርስቶስ ኃጢአትን ለማስወገድ እንደ መጣው እንደ በጉ እና ሙሽራይቱ ትኖረው ዘንድ እንደ መጣው እንደ ሙሽራው ተገልጧል።
4. በጉ ለቤዛነት ነው፣ ሙሽራው ለሰርጉ ነው።
5. ቤዛነት እንደ የእግዚአብሔር በግ በክርስቶስ ተፈጽሟል፣ ሰርጉም ክርስቶስ እንደሚመጣው ሙሽራ ሙሽራይቱን ሲወስድ ይከናወናል።
6. እንደ ሙሽራው፣ ክርስቶስ ሰርግ ሊኖረው ይገባል፤ የእኛ ስፍራ የሙሽራይቱ ነው፣ የሚመጣው ክርስቶስ ስፍራ የሙሽራው ነው።
7. በምድር ላይ እርሱን ለመገናኘት ሙሽራይቱን ለመሆን እየተዘጋጀን ነው፣ እርሱ ደግሞ እንደ ሙሽራው መጥቶ እኛን ለመገናኘት ተዘጋጅቶ በሦስተኛው ሰማይ በዙፋኑ ላይ ነው።
8. እርሱ እንደ ሙሽራ እየመጣ ነው፣ እኛ ደግሞ እንደ ሙሽራይቱ እየሄድን ነው—ማቴ. 25፥1።

*© 2025 Living Stream Ministry*

መልእክት ሦስት

## ኢየሱስ—በእግዚአብሔር የተሰጠው የንጉሡ-አዳኝ ስም
## እና
## አማኑኤል—በሰው የተጠራበት የንጉሡ-አዳኝ ስም

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ማቴ 1፥21፣ 23፤ 18፥20፤ 28፥20

I. **"ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ"—ማቴ 1፥21፡-**

ሀ. *ኢየሱስ* የሚለው የግሪኩ ስም፣ *ኢያሱ* የሚለው የዕብራይስጥ ስም አቻ ነው፣ ትርጓሜውም "ያህዌ አዳኙ" ወይም "የያህዌ ማዳን" ማለት ነው፤ ኢየሱስ ያህዌ አዳኛችንና ድነታችን መሆኑ ነው—ሮሜ 10፥12-13፤ 5፥10፤ ተዛ. ፊልጵ. 1፥19።

ለ. ያህዌ በራሱ የሚኖረውና ለዘላለም የሚኖረው ዘላለማዊው፣ ጥንት የነበረው፣ አሁን ያለው፣ ወደፊት ለዘላለም የሚኖረው እርሱ መሆኑን በማመልከት ኢየሱስ የሚለው ስም "እኔ እኔ ነኝ" ማለት የሆነውን የያህዌን ስም ያካትታል—ዘጸ. 3፥14፤ ራእ. 1፥4፡-

1. ያህዌ ብቸኛው እኔ ነኝ የሆነውና ከራሱ ውጭ በማንም ላይ የማይመረኮዘው ነው፤ "እርሱ እንደሆነ" እና እኛ "እንዳልሆንን" ለማመን የእምነት መንፈሳችንን ማንቀሳቀስ አለብን፤ እርሱ በሁሉ ነገር ብቸኛው፣ ልዩና ብቸኛው ነው፣ እኛ ደግሞ ምንም ነን—ዕብ. 11፥6።
2. እኔ ነኝ እንደመሆኑ፣ እርሱ ሁሉን-ያካተተው፣ የአዎንታዊ ነገር ሁሉ እና ሕዝቡ የሚያስፈልጋቸው ሁሉ እውነታ ነው—ዮሐ. 6፥35፤ 8፥12፤ 10፥14፤ 11፥25፤ 14፥6።
3. እኛ አማኞች የገንዘቡ መጠን የሚጻፍበት፣ ባዶ የተተወ የተፈረመበት ቼክ አለን ማለት እንችላለን፤ በሚያስፈልገን ሁሉ [ቼኩን] ልንሞላውም እንችላለን፤ የሚያስፈልገን ሁሉ፣ እንደ ብርሃን፣ ሕይወት፣ ኃይል፣ ጥበብ፣ ቅድስና ወይም ጽድቅ የመሳሰሉት ኢየሱስ ነው፤ የሚያስፈልገን ነገር ሁሉ በኢየሱስ ስም ውስጥ ይገኛል።

ሐ. ኢየሱስ ኢያሱአችን ነው፣ እንደ ኢያሱአችንም መልካም ምድራችን ወደሆነው እረፍት፣ ማለትም፣ ወደ ራሱ የሚያመጣን እርሱ ነው—ዕብ. 4፥8፤ ማቴ. 11፥28-29።

መ. የጌታ ስም፣ ማንነቱ፣ ሁሉን-ያካተተው የተቀመመው መንፈስ ነው—መኃ. 1፥3፤ ዘጸ. 30፥23-30፤ ፊልጵ. 1፥19።

ሠ. የኢየሱስ ስም ከስም ሁሉ በላይ ነው—2፥9-10፡-

1. የኢየሱስ ስም ወደ ውስጡ እንድናምንበት ነው—ዮሐ. 1፥12።
2. የኢየሱስ ስም ወደ ውስጡ እንድንጠመቅበት ነው—ሐዋ. 8፥16፤ 19፥5።
3. የኢየሱስ ስም እንድንድንበት ነው—4፥12።
4. የኢየሱስ ስም እንድንፈወስበት ነው—3፥6፤ 4፥10።
5. የኢየሱስ ስም እንድንታጠብበት፣ እንድንቀደስበት እና እንድንጸድቅበት ነው—1 ቆሮ. 6፥11።
6. የኢየሱስ ስም እንድንጠራው ነው—ሮሜ 10፥13፤ 1 ቆሮ. 1፥2፤ ሐዋ. 9፥14፤ ዘፍ. 4፥26።
7. መንፈስ እንድንተነፍሰው ሰማያዊው አየራችን ነው፤ የጌታን ስም ለመጥራት መንፈሳችንን በማንቀሳቀስ መንፈስን ወደ ውስጣችን እንተነፍሰዋለን፣ በዚህም መንፈስን እንቀበላለን—ዮሐ. 20፥22፤ ገላ. 3፥2፤ 1 ተሰ. 5፥17፤ ሰቆ. 3፥55-56፤ ከእንግሊዝኛው መዝሙር #255።

ረ. የጌታን ስም የመጥራት ዓላማ፡-

1. ለመዳን ነው—ሮሜ 10፥13።
2. ከጭንቀት፣ ከችግር፣ ከኃዘንና ከሕመም ለመዳን ነው—መዝ. 18፥6፤ 118፥5፡ 86፥7፤ 50፥15 81፥7፤ 116፥3-4።
3. በጌታ ርኅራኄ፣ በምሕረቱ ውስጥ ለመሳተፍ ነው—86፥5።
4. የጌታን ማዳን ለመካፈል ነው—116፥2፣ 4፤ 13፤ 17።
5. መንፈስን ለመቀበል ነው—ሐዋ. 2፥17፣ 21።
6. ለእርካታ መንፈሳዊውን ውኃ ለመጠጣትና መንፈሳዊውን ምግብ ለመመገብ ነው—ኢሳ. 55፥1-2፤6።
7. የጌታን ብልጥግናዎች ለመደሰት ነው—ሮሜ 10፥12፤ 1 ቆሮ. 12፥3፤ ዘዳ. 4፥7፡ መዝ. 145፥18።
8. ራሳችንን ለማነሳሳት ነው—ኢሳ. 64፥7።
9. የኢየሱስ ስም እንድንጸልይበት ነው—ዮሐ. 14፥13-14፤ 15፥16፤ 16፥24።
10. የኢየሱስ ስም እንድንሰበሰብበት ነው—ማቴ. 18፥20።
11. የኢየሱስ ስም አጋንንትን እንድናወጣበት ነው—ሐዋ. 16፥18።

12. የኢየሱስ ስም በድፍረት እንድንናገርበት ነው—9፥27።

ሰ. ሰይጣን የኢየሱስን ስም ይጠላዋል፡-

1. ሰይጣን የኢየሱስን ስም ለማጥቃት ሰዎችን ይጠቀማል—ተዛ. 26፥9።
2. አማኞች በዚያ ስም እንዳይሰብኩ ወይም እንዳያስተምሩ በመከልከል ሃይማኖተኞች የኢየሱስን ስም አጥቅተውታል—4፥17-18፤ 5፥40።
3. ሐዋርያት በተሰደዱ ጊዜ፣ ስለ ኢየሱስ ስም ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለተቆጠሩ ደስ አላቸው—ቁ. 41፤ 15፥26።

ሸ. ጌታ ኢየሱስ በፊልድልፍያ ያሉትን ድል ነሺዎች ስሙን ስላልካዱ አመሰገናቸው—ራእ. 3፥8፡-

1. የተመለሰችው ቤተ ክርስቲያን ፍጹም ለጌታ በመሆን ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ውጭ የሆኑትን ስሞች ሁሉ ትታለች።
2. ከጌታ ስም ውጭ የሆነ ማንኛውንም ስም በመውሰድ ቤተ ክርስቲያንን መከፋፈል መንፈሳዊ ዝሙት ነው፤ ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደታጨች ንጽሕት ድንግል (2 ቆሮ. 11፡2) ከባሏ ውጭ የሌላ ስም ሊኖራት አይገባም።

**II. "እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል...ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው"—ማቴ. 1፥23፡-**

ሀ. ኢየሱስ በእግዚአብሔር የተሰጠው የንጉሡ-አዳኝ ስም ነው፣ አማኑኤል ደግሞ በሰው የተጠራበት የንጉሡ-አዳኝ ስም ነው—ቁ. 23።

ለ. ማቴዎስ፣ ስለ አማኑኤል—ከእኛ ጋር ለመሆን ሥጋ ስለለበሰው አምላክ—የሚመለከት መጽሐፍ ነው—ቁ. 21-23።

ሐ. አማኑኤል ሁሉን-ያካተተ ነው—ፊልጵ. 1፥19፡-

1. እርሱ በመጀመሪያ አዳኛችን (ሉቃ. 2፥11)፣ ከዚያም ተቤዢያችን (ዮሐ. 1፥29፤ ሮሜ 3፥24)፣ ከዚያም ሕይወት ሰጪያችን (1 ቆሮ. 15፥45)፣ ከዚያም ሁሉን-ያካተተው፣ በውስጥ የሚኖረው መንፈስ ነው (ዮሐ. 14፥16-20፤ ሮሜ 8፥9-11)።
2. በእርግጥም፣ የመላው አዲስ ኪዳን ይዘት አማኑኤል ነው (ማቴ 1፥23፤ 18፥20፤ 28፥20፤ ራእ. 21፥3)፣ በክርስቶስ የሚያምኑ አማኞች ሁሉ፣ እንደ ክርስቶስ ብልቶች፣ የዚህ ታላቅ አማኑኤል፣ ብዙዎች የተካተቱበት ክርስቶስ ክፍል ናቸው (1 ቆሮ. 12፥12፤ ቆላ. 3፥10-11)።

መ. ተግባራዊው አማኑኤል እንደተጠናቀቀው ሦስታንድ አምላክ መገኘት በመንፈሳችን ያለው የእውነታ መንፈስ ነው፤ መገኘቱ ዕለት ዕለት ብቻ ሳይሆን አፍታ አፍታ በመንፈሳችን ውስጥ ሁልጊዜም ከእኛ ጋር ነው—ዮሐ. 1፥14፤ 14፥16-20፤ 1 ቆሮ. 15፥45፤ 2 ጢሞ. 4፥22፡-

1. እርሱ በስብሰባዎቻችን ከእኛ ጋር ነው—ማቴ. 18፥20።
2. እርሱ ሁልጊዜ ከእኛ ጋር ነው—28፥20።
3. እርሱ በመንፈሳችን ውስጥ ከእኛ ጋር ነው—2 ጢሞ. 4፥22፡-
   ሀ. መንፈሳችን ዛሬ የአማኑኤል ምድር ነው—ኢሳ. 8፥7-8።
   ለ. እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ስለሆነ፣ ጠላት የአማኑኤልን ምድር ሊቆጣጠረው አይችልም—ቁ 10፤ ተዛ. 1 ዮሐ. 5፥4፤ ዮሐ. 3፥6።
4. ለቅዱስ ቃሉ ትምህርት አብሮ በመሰብሰብ የሦስታንዱን አምላክ መገኘት መደሰት እንችላለን—ማቴ. 18፥20፤ 28፥20፤ መዝ. 119፥30፤ ሐዋ. 6፥4።
5. እንደ ሦስታንዱ አምላክ መገኘት በመንፈስ በኩል ጸጋና ሰላምን እንደሰታለን—ገላ. 6፥18፤ ሐዋ. 9፥31።
6. የመንፈስ መምራትና መመስከር መገኘቱ ናቸው—ሮሜ 8፥14፣ 16።
7. እንደ መንፈስ በመገኘቱ በኩል የሦስታንዱን አምላክ እደላ እንደሰታለን—2 ቆሮ. 13፥14።

ሠ. አማኑኤል ከሆነው ከክርስቶስ ጋር ለመኖር፣ እንደ ሦስታንዱ አምላክ መጠናቀቅ ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ በሆነው በመለኮታዊ መገኘቱ ውስጥ ልንሆን ያስፈልገናል —ገላ. 5፥25፡-

1. ከክርስቶስ ጋር ለመኖር፣ እኛም እንኖራለን፣ ነገር ግን በራሳችን ብቻ ሳይሆን ክርስቶስ በውስጣችን እና እንደ አማኑኤል ከእኛ ጋር በመኖሩ ነው፤ ሦስታንዱ አምላክ ራሱን ወደ ማንነታችን ውስጥ የማደል ውጥኑን ከእኛ ውጭ ሊያጠናቅቀው አይችልም፤ ስለዚህ፣ ከእኛ ጋር መሆኑ ውስጣዊ መሆን አለበት—2፥20።
2. አማኑኤል ሕይወታችንና ማንነታችን ነው፤ እኛም እንደ አንድ ማንነት ከእርሱ ጋር የምንኖር የእርሱ ክፍል ነን፤ ድላችን በአማኑኤል፣ በኢየሱስ መገኘት ላይ ይመረኮዛል።

3. የጌታ መገኘት ካለን፣ ጥበብ፣ አስተዋይነት፣ አርቆ አሳቢነትና ስለነገሮች ውስጣዊ እውቀት አለን፤ የጌታ መገኘት ሁሉ ነገራችን ነው—2 ቆሮ. 2፥10፤ 4፥6-7፤ ገላ. 5፥25፤ ዘፍ. 5፥22-24፤ ዕብ. 11፥5-6።

ረ. እንደ መልካሚቱ ምድር እውነታ ሁሉን-ወዳካተተው ክርስቶስ ውስጥ መግባት፣ የራሳችን ማድረግና መደሰት ከፈለግን፣ ያንን በጌታ መገኘት ማድረግ አለብን፤ ጌታ ለሙሴ "ህልዎቴ ከአንተ ጋር ይሄዳል፤ ዕረፍትም እሰጥሃለሁ" (ዘጸ. 33፥14 አ.መ.ት.) ብሎ ቃል ገባለት፤ የእግዚአብሔር መገኘት መንገዱ፣ ሕዝቡ ሊወስዱት የሚገባቸውን መንገድ የሚያሳይ "ካርታ" ነው፡-

1. ሁሉን-እንዳካተተው ምድር ክርስቶስን ለእግዚአብሔር ግንባታ በሙላት ለማትረፍ እና የራሳችን ለማድረግ፣ የእግዚአብሔር መገኘት ለሁሉም ነገር መስፈርት የመሆኑን መርህ መያዝ አለብን፤ የምናደርገው ነገር ምንም ይሁን ምን፣ የእግዚአብሔር መገኘት ያለን ወይም የሌለን ስለመሆኑ ትኩረት መስጠት አለብን፤ የእግዚአብሔር መገኘት ካለን፣ ሁሉም ነገር አለን፣ የእግዚአብሔርን መገኘት ካጣን ግን ሁሉንም ነገር እናጣለን—ማቴ. 1፥23፤ 2 ጢሞ. 4፥22፤ ገላ. 6፥18፤ መዝ. 27፥4፣ 8፤ 51፥11።
2. የጌታ መገኘት፣ የጌታ ፈገግታ ገዢው መርህ ነው፤ በቀጥተኛው፣ በመጀመሪያው የጌታ መገኘት መጠበቅን፣ መገዛትን፣ መተዳደርንና መመራትን መማር አለብን—27፥8፤ 80፥3፣ 7፣ 17-19።
3. እንደ በሰለው ሕይወት የሚነግሥ ገጽታ ወኪል፣ ከጌታ ሥልጣን፣ ብልጽግናና በረከት ጋር ዮሴፍ የጌታን መገኘት ተደሰተ—ዘፍ. 39፥2-5፣ 21፤ ሐዋ. 7፥9።
4. ሙሴ ለእግዚአብሔር ልብ እጅግ የቀረበና በእግዚአብሔር ልብ መሠረት የሆነ ሰው ነበር፤ ስለዚህ፣ የእግዚአብሔር መገኘት በሙላት ነበረው—ዘጸ. 33፥11።
5. ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ መላው ማንነቱ ጠቋሚ በክርስቶስ ዓይኖች ውስጥ በተገለጠው በክርስቶስ መገኘት ውስጥ የኖረና የተንቀሳቀሰ ሰው ነበር—2 ቆሮ. 2፥10።
6. ድል ለመንሣት፣ አሸናፊ ለመሆን፣ ቅዱስ ለመሆን እና መንፈሳዊ ለመሆን በልጅነቴ የተለያዩ መንገዶችን ተምሬአለሁ። ሆኖም፣ ከእነዚህ መንገዶች የትኛውም አልሠራም...የጌታ መገኘት እንጂ ምንም ነገር አይሠራም። እርሱ ከእኛ ጋር መሆኑ ሁሉ ነገር ነው።"—*Life-study of Joshua,* 2nd ed., p. 50.

ሰ. መላው አዲስ ኪዳን አማኑኤል ነው፣ አሁን እኛም በአዲሱ ሰማይና በአዲሱ ምድር ለዘላለም በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የሚጠናቀቀው የዚህ ታላቅ አማኑኤል ክፍል ነን፤ አዲስ ኪዳን "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር" በሆነው በአምላክ ሰው ይጀምርና "እግዚአብሔር በዚያ አለ" በሆነው በታላቁ አምላክ-ሰው በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ይጠናቀቃል—ማቴ. 1፥23፤ 1 ቆሮ. 6፥17፤ ሐዋ. 9:4፤ 1 ጢሞ. 3፥15-16፤ ራእ. 21፥3፣ 22፤ ሕዝ. 48፥35።

© 2025 Living Stream Ministry

**መልእክት አራት**

**ክርስቶስ በሂደት እንዳለፈው ሦስታንዱ አምላክ ማዕከል**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ማቴ. 28፥19፤ 1 ቆሮ. 15፥45፤ 2 ቆሮ. 3፥17፤ 13፥14

I. **የመለኮታዊው ሥላሴ ግልጹ መገለጥ ያለው በማቴዎስ 28፥19 ነው፦ "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ ወደ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም ውስጥ እያጠመቃችኋቸው፣ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" (*ከሪካቨሪ ቨርዥን መጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታ የተተረጎመ*)፡**

ሀ. "ወደ...ስም ውስጥ" የሚለው ማንነትን ያመለክታል፦

1. መጠመቅ ማለት (ማንነትን ወደ ሚያመለክተው) ወደ አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ስም ውስጥ፣ በሂደት ካለፈው ሦስታንዱ አምላክ ጋር ወዳለ ሕይወታዊ ጥምረት ውስጥ መጠመቅ ነው።
2. በ 28፥19 ያለው *ወደ...ውስጥ* የሚለው በሮሜ 6፥3፤ በገላትያ 3፥27 እና በ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥13 እንዳለው ጥምረትን ይጠቁማል።
3. ሰዎችን ወደ ሦስታንዱ አምላክ ስም ውስጥ ማጥመቅ፣ እነርሱን ከእርሱ ጋር ወዳለ መንፈሳዊና ምሥጢራዊ ጥምረት ውስጥ ማጥመቅ ነው።
4. በማቴዎስ 28፥19 ለሥላሴ አንድ ስም አለ፦

   ሀ. ስሙ ለማንነቱ የመለኮታዊ አቻ ጥቅል ድምር ነው።

   ለ. አማኞችን ወደ ሥላሴ ስም ውስጥ ማጥመቅ እነርሱን ሦስታንዱ አምላክ ወደሆነው ነገር ሁሉ ውስጥ ማጥመቅ ነው።

ለ. እግዚአብሔር ሦስት-በ-አንድ ነው—2 ቆሮ. 13፥14፦

1. በማቴዎስ 28፥19 ጌታ ስለ ሦስት ማንነቶች—ስለ አብ፣ ስለ ወልድ እና ስለ መንፈስ ቅዱስ—ይናገራል።
2. እዚህ ጋር ስለ አብ፣ ስለ ወልድ እና ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር፣ በመጀመሪያው ጽሑፍ *ስም* የሚለው በነጠላ ቁጥር ተቀምጧል።
3. ይህ ማለት አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ሦስት ናቸው፤ ስሙ ግን አንድ ነው።
4. ለሦስት ማንነቶች አንድ ስም መሆኑ በእውነቱ ምሥጢራዊ ነው፣ እግዚአብሔር ሦስት-በ-አንድ መሆኑንም ይገልጣል።
5. ይህ ስም ሦስቱንም—አብን፣ ወልድን እና መንፈስ ቅዱስን—ያካትታል፣ እግዚአብሔር ሦስት-በ-አንድ መሆኑም ይገልጣል።
6. ምንም እንኳ እግዚአብሔር ልዩና ብቸኛ በሆነ መንገድ አንድ ቢሆንም፣ ነገር ግን ሦስት ማንነቶች—አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ—አሉ።

II. **በክርስቶስ እንደሚያምኑ ሰዎች፣ በሂደት ወዳለፈው ሦስታንዱ አምላክ ውስጥ ተጠምቀናል፦**

ሀ. በማቴዎስ 28፥19 የተሰጠው ትእዛዝ ጌታ ኢየሱስ፣ በሂደት ያለፈው የሦስታንዱ አምላክ መጠናቀቅ ወደሆነው ወደ ትንሣኤ ውስጥ ከገባ በኋላ በእርሱ የተሰጠ ነበር።

ለ. ሦስታንዱ አምላክ በተሠግዎ በጀመረው፣ የሰብዕና ኑሮንና ስቅለትን ባካተተውና በትንሣኤ በተጠናቀቀው ሂደት አልፏል።

ሐ. የሦስታንዱ አምላክ አካል መልበስ የሆነው ክርስቶስ በትንሣኤ ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ—1 ቆሮ. 15፥45፤ 2 ቆሮ. 3፥17።

መ. ይህ መንፈስ፣ አማኞች ወደ መለኮታዊው ሥላሴ ውስጥ ይጠመቁ ዘንድ የሦስታንዱ አምላክ መጠናቀቅ ነው።

ሠ. በአንድ በኩል፣ ማቴዎስ 28፥19 ስለ አብ፣ ስለ ወልድ እና ስለ መንፈስ ቅዱስ ይናገራል፤ በሌላ በኩል፣ በዚህ ጥቅስ ውስጥ አንድ ስም ብቻ አለ—የአብ፣ የወልድ እና የመንፈስ ቅዱስ ስም።

ረ. ወደ ሥላሴ ማንነት ውስጥ መጠመቅ በሂደት ያለፈው የሦስታንዱ አምላክ ከፍተኛ እና የመጨረሻ መጠናቀቅ በሆነው ሁሉን ባካተተው፣ በተጠናቀቀው መንፈስ መጠመቅ ነው፦

1. ይህ ማለት ወደ አብ ብልጥግናዎች ውስጥ፣ ወደ ወልድ ብልጥግናዎች ውስጥና ወደ መንፈስ ብልጥግናዎች ውስጥ መጠመቅ ነው።
2. እንደተጠመቁ ሰዎች፣ አሁን ከሦስታንዱ አምላክ ጋር በሕይወታዊ ጥምረት ውስጥ ነን፤ ስለዚህ፣ አብ ያለው ሁሉ፣ ወልድ ያለው ሁሉ እና መንፈስ ያለው ሁሉ የእኛ ሆኗል።

ሰ. ወደ ሦስታንዱ አምላክ ስም ውስጥ መጠመቅ ከእርሱ ጋር ወዳለ ወደ ምሥጢራዊ ጥምረት ውስጥ መጨመር እና እግዚአብሔር የሆነውን ሁሉ ወደ ማንነታችን ውስጥ መውሰድ ነው።

**III. ክርስቶስ በሂደት ያለፈው የሦስታንዱ አምላክ ማዕከል ነው—2 ቆሮ. 13፥14፦**

*ሀ. በሂዳት ያለፈው* የሚለው ሦስታንዱ አምላክ ያለፈባቸውን ወሳኝ እርምጃዎች ያመለክታል፦

1. ከተሠግዎው በፊት እግዚአብሔር መለኮታዊው ባሕርይ እንጂ የሰብዕና ባሕርይ ስላልነበረው በሂደት ያላለፈ ነበር፤ ነገር ግን በተሠግዎ፣ በሰብዕና ኑሮ፣ በስቅለት፣ በትንሣኤ እና በዕርገት፣ ሦስታንዱ አምላክ በሂደት አልፏል፣ ተጠናቆማል።
2. በራእይ፣ ሦስታንዱ አምላክ መለኮትነት፣ ሰብዕና፣ የሰብዕና ኑሮ፣ ሁሉን-ያካተተ ሞት፣ ኃይለኛው ትንሣኤ እና ሁሉን ጥሶ የሚወጣው ዕርገት ያለው በሂደት ያለፈውና የተጠናቀቀው ነው—1፥4-5።

ለ. በሂደት ያለፈውና የተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ መንፈስ ነው—22፥17፤ ዮሐ. 7፥39፦

1. መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ ስያሜዎች ንጥረ ነገሮች ሁሉ ጥቅል ድምር ነው—ማቴ. 3፥16፤ 10፥20፤ ሉቃ. 1፥35፤ 4፥18፤ ሮሜ 8፥9፤ ገላ. 4፥6።
2. በሂደት እንዳለፈውና እንደተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ መጠናቀቅ፣ መንፈስ የእግዚአብሔር አዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ በረከት ነው—ገላ. 3፥14።

ሐ. በራእይ መጽሐፍ ያለው ሦስታንዱ አምላክ የሚገናባውና የተገነባው አምላክ ነው—21፥18-19፣ 21፦

1. መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠናቀቀው በመጀመሪያ የነበረውን እግዚአብሔርን ራሱ በሆነችው በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ነው—ዘፍ. 1፥1፤ ራእ. 21፥10፦
   ሀ. ልዩና ብቸኛው አምላክ በስተመጨረሻ ለዘላለማዊው መገለጡ ከተማ ወደ መሆን ይተሊቃል፣ ይስፋፋልም።
   ለ. በኢኮኖሚው እግዚአብሔር አዲሲቱን ኢየሩሳሌም ሆኗል—ቁ. 10።
   ሐ. በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ሦስታንዱ አምላክ ወደ ዋጃቸው ሰዎች ውስጥ ተሠርቷል—ቁ. 18-19፣ 21።
2. አዲሲቱን ኢየሩሳሌም የሆነው ሦስታንዱ አምላክ የሚገነባውና የተገነባው አምላክ ሆኗል—2 ሳሙ. 7፥12፣ 14፤ ማቴ. 16፥18፤ ኤፌ. 3፥17፦
   ሀ. በሂደት ያለፈውና የተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ እንደ ምንጭ፣ እንደ ንጥረ ነገር እና እንደ ውስጠ ነገር ራሱን ወደ ማንነታችን ውስጥ በመገንባት ቤተ ክርስቲያንን እየገነባ ነው—ቁ. 17።
   ለ. እግዚአብሔር በክርስቶስ ራሱን ወደ ማንነታችን ውስጥ መገንባትና እኛን ወደ ማንነቱ ውስጥ መገንባት የሆነውን መሻቱን እየፈጸመ ነው፤ በስተመጨረሻ፣ የዚህ ግንባታ ውጤት አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ትሆናለች—ራእ. 21፥2፣ 10።

መ. በራእይ መጽሐፍ፣ ለመለኮታዊ እደላ የሆነው የመለኮታዊው ሥላሴ የተጠናቀቀ መገለጥ አለን—22፥1-2፤ 7፥17፤ 21፥6፤ ዮሐ. 4፥14፦

1. መለኮታዊው እደላ እንደ ሕይወታቸው፣ እንደ የሕይወት አቅርቦታቸው እና እንደ ሁሉ ነገራቸው እግዚአብሔር ወደ መረጣቸው እና ወደ ዋጃቸው ሕዝቡ ውስጥ ራሱን ማስተላለፉ ነው—2 ቆሮ. 13፥14።
2. በመለኮታዊው እደላ ውስጥ አብ ምንጭ ነው፣ ወልድ ፍልቅ ነው፣ መንፈስ ፍሰት ነው።

© 2025 Living Stream Ministry

መልእክት አምስት

## ክርስቶስ ዕረፍት እንደሚሰጠን ማንነት

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ዘፍ. 1፥26፤ 31—2፥2፤ ማቴ. 11፥28-30፤ ዘጸ. 31፥12-17

**I. "እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፣ ወደ እኔ ኑ፣ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፣ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፣ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና"—ማቴ. 11፥28-30፡-**

ሀ. እዚህ ጋር የተጠቀሰው ድካም የሕግ ትእዛዛትን እና ሃይማኖታዊ ደንቦችን ለመጠበቅ የሚደረገውን ልፋት የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን፣ በማንኛውም ሥራ ስኬታማ ለመሆን ያለውንም ልፋት ያመለክታል፤ ስለዚህም፣ ማንኛውም የሚደክም ሰው ሁሌም ሸክሙ የከበደበት ነው።

ለ. ጌታ ለአብ መንገድ እውቅና በመስጠትና መለኮታዊውን ኢኮኖሚ በማወጅ አብን ካመሰገነ በኋላ (ቁ. 25-27)፣ ለማረፍ ወደ እርሱ እንዲመጡ እንዲህ ዓይነት ሰዎችን ጠራ።

ሐ. ዕረፍት ከሕግ ወይም ከሃይማኖት ወይም ከማንኛውም ዓይነት ሥራ ወይም ኃላፊነት በታች ካለው ድካም እና ሸክም ነጻ መውጣትን የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን፣ ፍጹም ሰላምን እና ሙሉ እርካታንም ያመለክታል።

መ. የጌታን ቀንበር መሸከም የአብን ፈቃድ መሸከም ነው፤ በሕግ ወይም በሃይማኖት ግዴታ ቁጥጥር ሥር መሆን፣ ወይም በማንኛውም ሥራ ባርነት ሥር መውደቅ ሳይሆን በአብ ፈቃድ መገደብ ነው።

ሠ. ጌታ ለአባቱ ፈቃድ እንጂ ለሌላ ነገር ግድ ባለመሰኘት እንዲህ ዓይነቱን ሕይወት ኖሯል (ዮሐ. 4፥34፤ 5፥30፤ 6፥38)፤ ጌታ ሙሉ በሙሉ ለአብ ፈቃድ ራሱን አስገዛ (ማቴ. 26፥39፣ 42)፤ ስለዚህ፣ ከእርሱ እንድንማር ይጠይቀናል።

1. አማኞች የጌታን ቀንበር—የእግዚአብሔርን ፈቃድ—በመሸከም እና በእርሱ ሞዴል መሠረት ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ በመድከም ጌታን በመንፈሳቸው ይመስሉታል—11፥29፤ 1 ጴጥ. 2፥21።
2. በሕይወቱ ሁሉ ለአብ ተገዢና ታዛዥ የነበረው ጌታ የመገዛትና የመታዘዝ ሕይወቱን ሰጥቶናል—ፊልጵ. 2፥5-11፤ ዕብ. 5፥7-9።
3. ክርስቶስ የመጀመሪያው አምላክ ሰው ነበር፣ እኛ ደግሞ ብዙ አምላክ-ሰዎች ነን፤ ለእግዚአብሔር ባለው ፍጹም መገዛትና በእግዚአብሔር ፈጽሞ በመርካቱ ከእርሱ መማር አለብን።
4. ፈቃዱን ማድረግ እንድንችል እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን በእኛ እያደረገ ነው (13፥20-21)፤ እግዚአብሔር ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእኛ ይሠራል (ፊልጵ. 2፡13)።

ረ. የዋህ ወይም ለስላሳ መሆን ማለት ለተቃውሞ ምላሽ አለመስጠት ነው፤ ትሑት መሆን ማለት ለራስ-ክብር ያለው አለመሆን ማለት ነው፤ በተቃውሞዎች ሁሉ ውስጥ ጌታ የዋህ ነበር፣ ተቀባይነት በማጣት ውስጥም በልቡ ትሑት ነበር።

ሰ. ለራሱ ምንም ነገር ማድረግ ሳይፈልግ ወይም ለራሱ ምንም ነገር ማግኘትን ሳይጠብቅ ራሱን ሙሉ በሙሉ ለአባቱ ፈቃድ አስገዛ፤ ስለዚህ፣ ሁኔታው ምንም ይሁን ምን በልቡ ዕረፍት ነበረው፤ በአብ ፈቃድ ሙሉ በሙሉ የረካ ነበር።

ሸ. የጌታን ቀንበር በመሸከምና ከእርሱ በመማር የምናገኘው ዕረፍት ለነፍሳችን ነው፤ ውስጣዊ ዕረፍት ነው፤ ይህ ዕረፍት በባሕርይ ውጫዊ የሆነ ብቻ አይደለም።

ቀ. ከጌታ የምንማረው በተፈጥሯዊ ሕይወታችን ሳይሆን በምሳሌው መሠረት፣ በትንሣኤ እንደሆነው ሕይወታችን በጌታ ነው—ኤፌ. 4፥20-21፤ 1 ጴጥ. 2፥21።

በ. የጌታ ቀንበር የአብ ፈቃድ ነው፣ ሸክሙም የአብን ፈቃድ የማከናወን ሥራ ነው፤ እንዲህ ያለው ቀንበር መራራ ሳይሆን ልዝብ ነው እና እንዲህ ያለው ሸክም ከባድ ሳይሆን ቀሊል ነው።

ተ. *ቀሊል* ለሚለው የግሪኩ ቃል ትርጉም "ለአጠቃቀም ተስማሚ" ነው፤ ስለዚህ፣ ከባድ፣ አስቸጋሪ፣ የሚጎዳ፣ የሚያስመርር ከመሆን በተቃራኒ መልካም፣ ቸር፣ ለስለስ ያለ፣ ለዘብ ያለ፣ ቀላል፣ ደስ የሚያሰኝ ማለት ነው።

ቸ. የጌታን ቀንበር (የአብን ፈቃድ) በላያችን ከተሸከምንና ከእርሱ ከተማርን፣ ለነፍሳችን ዕረፍት እናገኛለን፤ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ቀንበር እንደዚህ ነው፤ በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ ሁሉም ነገር ከባድ ሸክም ሳይሆን ድሰታ ነው።

**II. በዘጸአት 31፥12-17 የእግዚአብሔርን ማደሪያ ስፍራ በተመለከተ ከረጅም ዘገባ በኋላ ሰንበትን የመጠበቅ ትእዛዝ ድግግሞሽ አለ፤ በቆላስይስ 2፥16-17 መሠረት ክርስቶስ የሰንበት ዕረፍት እውነታ ነው፤ እርሱ ፍጹምነታችን፣ ዕረፍታችን፣ ጸጥታችንና ሙሉ እርካታችን ነው—ዕብ. 4፥7-9፤ ኢሳ. 30፥15፡-**

ሀ. ሰንበትን በተመለከተ የገባው ሃሳብ ለማደሪያው ድንኳን የግንባታ ሥራ ትእዛዝን የመከተሉ ሃቅ ጌታ ለእርሱ ሲሠሩ ሳሉ ከእርሱ ጋር እንዴት እንደሚያርፉ ለገንቢዎቹ፣ ለሠራተኞቹ እየነገረ እንደነበር ያመለክታል።

ለ. ለጌታ እንዴት እንደምንሠራ ብቻ የምናውቅ ነገር ግን ከእርሱ ጋር እንዴት እንደምናርፍ የማናውቅ ከሆንን፣ ከመለኮታዊው መርህ በተጻራሪ እየሠራን ነው፡-

1. ሥራውን ስለጨረሰና ስለረካ እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን አረፈ፤ ሰው የእግዚአብሔር መልክ ስለነበረውና ለጠላቱ፣ ለሰይጣን መሸነፍ ሥልጣኑ ሊንቀሳቀስ ስለነበር፣ የእግዚአብሔር ክብር ተገልጦ ነበር፤ ሰው እግዚአብሔርን እስከገለጠና የእግዚአብሔርን ጠላት እስካስወገደ ድረስ እግዚአብሔር ይረካል፣ ማረፍም ይችላል—ዘፍ. 1፥26፣ 31—2፥2።
2. በኋላ፣ ሰባተኛው ቀን ሰንበት ተብሎ ታስቧል (ዘጸ. 20፡8-11)፤ የእግዚአብሔር ሰባተኛ ቀን የሰው የመጀመሪያ ቀን ነበር።
3. እግዚአብሔር ለሰው ድሰታ ሁሉን ነገር አዘጋጅቶ ነበር፤ ሰው ከተፈጠረ በኋላ በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ አልተሳተፈም፤ ወደ የእግዚአብሔር ዕረፍት ውስጥ ገባ።
4. ሰው የተፈጠረው በመጀመሪያ ለመሥራት ሳይሆን በእግዚአብሔር ለመርካትና ከእግዚአብሔር ጋር ለማረፍ ነበር (ተዛ. ማቴ. 11፥28-30)፤ ሰንበት ለሰው ተፈጠሯል እንጂ ሰው ለሰንበት አልተፈጠረም (ማር. 2፡27)።

ሐ. ዘጸአት 31፥17 "እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን በስድስት ቀን ስለ ፈጠረ፣ በሰባተኛውም ቀን ከሥራው ስላረፈና ስለ ተነፈሰ" ይላል፡-

1. ሰንበት ለእግዚአብሔር ዕረፍት ብቻ ሳይሆን የሚያድሰውም ነበር።
2. እግዚአብሔር የመፍጠር ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ ዐረፈ፤ የእጆቹን ሥራ፣ ሰማያትን፣ ምድርን እና ሕያውየሆኑትን ነገሮች ሁሉ፣ በተለይም ሰውን ተመለከተና "እጅግ መልካም" አለ (ዘፍ. 1፥31)።
3. እግዚአብሔር በሰው ታድሷል፤ እግዚአብሔር ሰው ከእርሱ ጋር ኅብረት ማድረግ እንዲችል ሰውን በመልኩ ከመንፈስ ጋር ፈጠረው፤ ስለዚህ፣ ሰው እግዚአብሔርን የሚያድስ ነበር—ቁ. 26፤ 2፥7፤ ተዛ. ዮሐ. 4፥31-34።
4. እግዚአብሔር ሰውን ከመፍጠሩ በፊት "ያላገባ" ነበር (ተዛ. ዘፍ. 2፡18፣ 22)፤ ሰው እርሱን እንዲቀበል፣ እርሱን እንዲወድ፣ በእርሱ እንዲሞላ እና ሚስቱ ለመሆን እርሱን እንዲገልጥ ፈልጎ ነበር (1 ቆሮ. 11፡2፤ ኤፌ. 5፡25)፤ በወደፊት ዘላለም እግዚአብሔር ሚስት፣ የበጉ ሚስት ተብላ የተጠራችው አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ይኖረዋል (ራእ. 21፡9-10)።
5. ሰው የእግዚአብሔርን ጥም ለመቁረጥና እርሱን ለማርካት እንደሚያድስ መጠጥ ነበር፤ እግዚአብሔር ሥራውን ሲጨርስና ማረፍ ሲጀምር፣ ባልንጀራው የሆነ ሰው ነበረው።
6. ለእግዚአብሔር ሰባተኛው ቀን የዕረፍትና የመታደስ ቀን ነበረ፤ ሆኖም፣ የእግዚአብሔር ባልንጀራ ለሆነው ለሰው የዕረፍትና የመታደስ ቀን የመጀመሪያው ቀን ነበር፤ የሰው የመጀመሪያው ቀን የድሰታ ቀን ነበረ።

መ. ድሰታ እስከሚኖረን ድረስ እግዚአብሔር እኛን እንድንሠራ አለመጠየቁ መለኮታዊ መርህ ነው፤ ከእርሱ ጋር መሥራት የምንችለው ከእርሱ ጋርና የእርሱ ሙሉ ድሰታ ከኖረን በኋላ ነው፡-

1. ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት እንደምንደሰት፣ እግዚአብሔር ራሱን እንዴት እንደምንደሰትና በእግዚአብሔር እንዴት እንደምንሞላ የማናውቅ ከሆነ፣ እንዴት ከእርሱ ጋር እንደምንሠራና በመለኮታዊው ሥራው ውስጥ ከእርሱ ጋር አንድ እንደምንሆን አናውቅም፤ እግዚአብሔር በሥራው የፈጸመውን ሰው ይደሰታል።
2. በበዓለ ኀምሳ ቀን ደቀ መዛሙርቱ በመንፈስ ተሞሉ፣ ይህም ማለት በጌታ ድሰታ ተሞሉ ማለት ነው፤ በመንፈስ ተሞልተው ስለነበር፣ ሌሎች በወይን ጠጅ የሰከሩ መሰላቸው—ሐዋ. 2፥4፤ 12-13።
3. በእርግጥ፣ በሰማያዊው የወይን ጠጅ ድሰታ ተሞልተው ነበር፤ በዚህ ድሰታ ከተሞሉ በኋላ ብቻ ከእግዚአብሔር ጋር በአንድነት አብረው መሥራት ጀመሩ፤ በዓለ ኀምሳ የስምንተኛው ሳምንት የመጀመሪያው ቀን ነበር፤ ስለዚህ፣ የበዓለ ኀምሳ ቀንን በተመለከተ፣ የመጀመሪያውን ቀን መርህ እናያለን።
4. በእግዚአብሔር ዘንድ የመሥራትና የማረፍ ጉዳይ ነው፤ በሰው ዘንድ የማረፍና የመሥራት ጉዳይ ነው።

ሠ. የማደሪያውን ድንኳን በመገንባት ሥራ እንደተመሰለው ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባት የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ሥራ ስንሠራ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደሆንንና እርሱ እንደሚያስፈልገን የሚያሳይ ምልክት ሊኖረን ይገባል፤ ያኔ ለእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ በመሆን ከእርሱ ጋር መሥራት እንችላለን፤ ለመሥራት ብርታታችንና ለመድከም ኃይላችን ይሆንልናል፡-

1. እኛ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነን፣ እርሱን ለማክበር ለእርሱ መሥራት እንችል ዘንድ እርሱ ድሰታችን፣ ብርታታችን፣ ኃይላችን እና ሁሉ ነገራችን ሊሆን እንደሚያስፈልገን ምልክት ሊኖረን ይገባል።
2. ሰንበት ማለት ለእግዚአብሔር ከመሥራታችን በፊት እግዚአብሔርን መደሰትና በእርሱ መሞላት ያስፈልገናል ማለት ነው፤ ጴጥሮስ በውስጥ በሚሞላው እግዚአብሔር፣ በውስጥ በሚሞላው መንፈስ ወንጌል ሰበከ፤ ስለዚህ፣ ጴጥሮስ

የእግዚአብሔር አብሮ ሠራተኛ እንደነበረና የወንጌል ስብከቱ ለእግዚአብሔር ክብር እንደነበር ምልክት ነበረው—ቁ. 14።

3. እንደ የእግዚአብሔር ሕዝብ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እንደምናርፍ፣ እግዚአብሔርን እንደምንደሰትና መጀመሪያ በእግዚአብሔር እንደምንሞላ፣ ከዚያም በሚሞላን በራሱ እንደምንሠራ ምልክት ሊኖረን ይገባል፤ በተጨማሪም፣ ከእግዚአብሔር ጋር የምንሠራ ብቻ ሳንሆን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ በመሆን እንደሚሠሩ ሰዎች እንሠራለን።
4. ለእግዚአብሔር ሕዝብ ባለን ንግግር፣ ቃሉን ለማገልገል ጌታችን ብርታታችን፣ ኃይላችንና ሁሉ ነገራችን እንደሆነ ምልክት እንዲኖረን ሁልጊዜ መፈለግ አለብን—2 ቆሮ. 13፡3፤ ሐዋ. 6፡4።

ረ. ሰንበትን መጠበቅ እግዚአብሔርን መጀመሪያ በመደሰትና በእርሱ በመሞላት፣ ከዚያም ለእርሱ፣ ከእርሱ ጋርና ከእርሱ ጋር አንድ በመሆን መሥራት እንዳለብን ለእግዚአብሔር የሚያረጋግጥ ዘላለማዊ ስምምነት ወይም ቃል ኪዳን ነው—ዘጸ. 31፡16፦

1. ጌታን በመጠጣትና በመብላት ሳንወስደውና ሳንደሰተው በራሳችን ለእርሱ መሥራት ከባድ ጉዳይ ነው—ተዛ. 1 ቆሮ. 12፡13፤ ዮሐ. 6፡57።
2. ጴጥሮስ በበዓለ ኀምሳ ቀን ሲናገር ሳለ፣ በውስጥ ኢየሱስን እየተካፈለ፣ እርሱን እየጠጣና እየበላ ነበር።

ሰ. ሰንበት የመቀደስም ጉዳይ ነው (ዘጸ. 31፡13)፤ ጌታን ስንደሰትና ከእርሱ ጋር፣ ለእርሱና ከእርሱ ጋር አንድ በመሆን ስንሠራ ሳንጣጣር እንቀደሳለን፣ ተራ ከሆነ ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር እንለያለን፣ ሥጋዊና ተፈጥሯዊ የሆነ ነገርን ሁሉ ለመተካት በእግዚአብሔር ፈጽመን እንሞላለን።

ሸ. በቤተ ክርቲያን ሕይወት ውስጥ ጌታን መጀመሪያ ሳንደሰትና ከጌታ ጋር አንድ በመሆን ጌታን ሳናገለግል ብዙ ነገር ልናደርግ እንችላለን፤ እንደዚያ ዓይነት አገልግሎት መንፈሳዊ ሞትንና በአካሉ ውስጥ ያለ ኅብረት ማጣትን ያስከትላል (ቁ. 14-15)።

ቀ. ከእግዚአብሔር ማደሪያ ስፍራ ጋር የተገናኘ ነገር ሁሉ ወደ አንድ ነገር—ከጌታ ዕረፍትና መታደስ ጋር ወደ ሰንበት—ይመራናል፤ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት በማደሪያው ድንኳን ውስጥ ነን፣ የማደሪያው ድንኳንም ወደ ዕረፍት፣ ወደ እግዚአብሔር ዓላማና እርሱ ወደ ፈጸመው ነገር ድሰታ ይመራናል!

በ. የማደሪያው ድንኳንና በውስጡ ያሉት ዕቃዎች ሁሉ የግንባታ ሥራ (ጌታ ቤተ ክርስቲያንን የመገንባቱን ሥራ በምሳሌ የሚያሳየው) እግዚአብሔርን በመደሰት መጀመርና በየተወሰኑ ተከታታይ ጊዜያት እግዚአብሔርን በመደሰት መታደሶች መቀጠል አለበት፤ ለእግዚአብሔር የምንሠራው በራሳችን ብርታት ሳይሆን እርሱን በመደሰትና ከእርሱ ጋር አንድ በመሆን እንደሆነ ይህ ያመለክታል፤ ይህ በመንፈሳችን ውስጥ እንዳለው የውስጥ ዕረፍት በክርስቶስ የሰንበትን መርህ መጠበቅ ነው።

© 2025 Living Stream Ministry